Free digital copy from ServeNow

# ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች

ቤን ፎሊ

ServeNow

Free digital copy from ServeNow

*ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች*

*The Basic Things You Need to Know About The Church*
(Amharic)

ጸሓፊ፡ ቤን ፎሊ
አርታዒ፡ ላርስ ዴንበርግ

የቅጅ መብት © 2015 ሰርቭ ናው

በፈቃድ ጥቅም ላይ የዋለ፤ መብቱ የተጠበቀ

ISBN፡978-1-964796-21-5

የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ከማጥኛ ጽሑፍ ጋር፤ በቢብሊካ የታተመ ©1993፤2003

The Bible in Amharic©United Bible Societies 1962
Holy Bible, New Amharic Standard Version (አዲሱ መደበኛ ትርጉም).
Copyright © 2001 by Biblica, Inc.® በፈቃድ የተወሰደ: መብቱ በዓለም ዙሪያ የተጠበቀ ነው።

በሰርቭ ናው (*ServeNow*) የታተመ፣
1817 Austin Bluffs Parkway #110
Colorado Springs, CO. 80918, USA

Free digital copy from ServeNow

# ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች

## መግቢያ

በምድር ላይ ከሚገኘው ከየትኛውም ነገር በላይ እጅግ ውቧ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን "የቅዱሳን ስብስብ" ናት። በርግጥ ብዙ ችግሮች እና ስህተቶች ነበሯት፣ እስከ ስህተቶቿም ትቀጥላለች፤ ሆኖም ግን ለተጠራችበት ዐላማ ስትኖር እንደ ርሷ ያለ አንዳች ተቋም በምድር ላይ አይኖርም። ኢየሱስ "እመሠርታለሁ" ያላትም ናት። ዛሬ በምድር ላይ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራውም በቤተ ክርስቲያን በኩል ነው።

ግን ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት? ምንስ ለመፈጸም ተጠራች? ተግባሯንስ እንዴት ትፈጽማለች? ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ምን ትመስላለች?

## ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል

ኢየሱስ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ መጠቀሙን በወንጌላት የመጽሐፍ ቅዱሳችን ክፍል ውስጥ ከተጻፈበት ጊዜ አንስቶ ቃሉ ጥቅም ላይ ውሏል። በዐዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ እንኳ ወደ 79 ጊዜያት ተጠቅሷል። የዚህ ቃል የግሪክ አቻ ትርጉሙ ኤክሌሺያ ይባላል። ኤክሌሺያ ከሁለት ቃላት የተገኘ ሲሆን ከ"መጠራት" ወደ "መሰባሰብ" የሚል ትርጓሜ ይይዛል። ዐሳቡ ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስ አካላት እንዲሆኑ "የተጠሩት" (ከኃጢአት እና ከዓለም) ሰዎች የተዋቀረች መሆኗን ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች በስሙ፣ በባሕርዩ፣ በሥልጣኑ እና በኃይሉ "ይሰባሰባሉ" ደግሞም "ይመላለሳሉ"።

Free digital copy from ServeNow

## የቤተ ክርስቲያን መሰባሰቢያ ሥፍራ

በታሪክ፣ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ቦታዎች ወይም ሁኔታዎች አንድ ላይ ስትሰባሰብ ኖራለች። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ላይ ለተወሰኑ ጊዜያት በየምኩራቦች ከዚያም ቤት ውስጥ ይገናኙ ነበር። ዛሬ እንደ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች በምናስበው ውስጥ ደግሞም በማናቸውም እና በሁሉም ዐይነት ሥፍራዎች እንደ ጣሪያዎች፣ ዛፎች ሥር፣ በትምህርት ቤት ሕንጻዎች ውስጥ፣ በመኖሪያ ቤቶች፣ በሆቴሎች፣ በሲኒማ ቤቶች እና የሂንዱ ቤተ መቅደሶች ውስጥ የሚሰበሰቡ አብያተ ክርስቲያናት አሉ!

ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሚሰበሰቡበት ሥፍራ ሳትሆን የኢየሱስ ክርስቶስ አካላት የሆኑ እና በአንድነት የሚሰበሰቡ የሕዝብ ስብስብ ናት። በርግጥ፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች ለሕዝብ አምልኮ እንዲገነቡ የተደረገው ገና ክርስትና በንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ሥር የሮማ ግዛት ሕጋዊ ሃይማኖት እያለ ነበር።

## ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሥራ ላይ መዋሉ

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በማቴዎስ 16፡ 18 ላይ ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ መሢሑ መሆን በእምነት በተናገረ ጊዜ ኢየሱስ የሰጠው ምላሽ *እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም* (ማቴዎስ 16፡18) የሚል ነበር።

ይህ ማለት አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ሲያምን እና ሲቀበል እንዲሁም ኃጢአቱን ሲናዘዝ ኢየሱስ እየገነባው ያለው ማኅበረ ሰብ አካል ይሆናል።

በዓለም ዙሪያ ያሉ አማኞች ሁሉ ከሌሎች አማኞች ጋራ በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ አውድ ውስጥ

Free digital copy from ServeNow

ይሰበሰባሉ። የተለያዩ የአማኞች ስብሰባዎች በተለያዩ ቦታዎች ቢኖሩም በክርስቶስ ግን ሁላችንም አንድ አካል ነን። በሰማይ በኢየሱስ የተዋጁት ሁሉ በአንድነት እግዚአብሔርን በዙፋኑ ዙሪያ ያመልኩታል።

## አንድ ግለ ሰብ እንዴት የቤተ ክርስቲያን አባል ሊሆን ይችላል?

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ላይ መሳተፍ ብቻውን አንድን ሰው እውነተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል ሊያደርገው አይችልም። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ አባል መሆን እንኳን በራሱ በክርስቶስ በእውነት አምናለሁ ማለት አይደለም። ወላጆችህ አማኞች እና የቤተ ክርስቲያን አባላት ስለሆኑ ብቻ ወላጆችህ ወይም አያቶችህ የያዙትን እምነት አለህ ማለት አይደለም። ጥያቄው አንተ በርሱ በማመን የኢየሱስ ክርስቶስ ሆነሃል ወይ? ነው።

እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ንስሐ የገቡ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ፣ ዳግመኛ በመወለዳቸው እና በዚህም የርሱ የሆኑትን ሁሉ ያቀፈች ናት። እንድንረዳው የሚረዱን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ቤተክርስቲያን ብዙ የተለያዩ ምሳሌዎች አሉ። ጥቂቶቹን እነሆ

### *አካል*

ጳውሎስ ለኤፌሶን ላሉ አማኞች ሲጽፍ *ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት፤ ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው። ርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የርሱ ሙላቱ ናት* (ኤፌሶን 1:22 - 23)።

በቆሮንቶስ ለሚገኙ አማኞችም ስለ አካል ሲጽፍ *አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው* (1 ቆሮንቶስ 12:12)።

Free digital copy from ServeNow

አካል አንድ ቢሆንም ብዙ ብልቶች እንዳሉት ነገር ግን ብልቶች ሁሉ አንድ አካል እንደሚሆኑ ሁሉ በክርስቶስም ዘንድ እንዲሁ ነው። ይህ ተቃርኖ ሳይሆን አስደናቂ እውነታ ነው። በኢየሱስ ጌትነት እና አመራር ሥር ርስ በርሳችን በአንድነት መሥራታችን አስፈላጊ የሆነው ለዚሁ ነው። አንድ አካል መከፋፈል ወይም መገለል አይችልም ደግሞም የለበትም።

እያንዳንዱ ሥራውን የሚያከናውን አካል ለአጠቃላይ ጤና፣ እድገት እና ጥንካሬ አስፈላጊ ነው። 1 ጴጥሮስ 4:10-11 እንደሚለው *ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ ርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤ ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን።*

## *የክርስቶስ ሙሽሪት*

በኤፌሶን 5:25-27 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የሁለት መሽሮችን ንጽጽር ያቀርባል፤ *ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ ርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።*

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በዮሐንስ 14:2-4 ላይ ቃል ሲገባ ወደ ሰማይ ተመልሶ ሊሄድ እንደሚገባውና ሥፍራም ሊያዘጋጅላቸው እንደሚሄድ ይናገራል። አክሎም አንድ ቀን ተመልሶ ሲመጣ ከራሱ ጋር እንዲኖሩ እንደሚወስዳቸው ቃል ገብቶላቸዋል። እንደ አይሁዳዊነታቸው ኢየሱስ

Free digital copy from ServeNow

የተጠቀመውን የዕብራውያኑ የጋብቻን ቋንቋ እና ምሳሌ ደቀ መዛሙርቱ ተረድተውታል።

በአይሁዳዊያን ባሕል ሙሽራ እና ሙሽሪት ከመጋባታቸው በፊት ባልየው ለርሱ እና ለሚስቱ የሚሆን የመኖሪያ ሥፍራ ያዘጋጅላቸዋል፤ በአብዛኛው ከአባቱ ቤት ጋራ የተያያዙ የተለያዩ የመኖሪያ ክፍሎችን ይገነባል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሙሽሪት ራሷን ለ"ትልቁ ቀን" ማዘጋጀት አለባት። በማንኛውም ጊዜ ሙሽራው ሊመጣላት ስለሚችል ርሷ ሁል ጊዜ ዝግጁ መሆን አለባት! ትክክለኛው የሰርጉ ቀን አስቀድሞ በሙሽራው እና በሙሽሪት አይወሰንም፤ ነገር ግን ጊዜው ሲደርስ የሚወስነው የሙሽራው አባት ነው።

በተመሳሳይ መልኩ በማንኛውም ጊዜ ሊሆን ለሚችለው ለኢየሱስ ዳግም መምጣት ዝግጁ መሆን አለብን። የእኛ ሥራ በምድር ላይ ለዘላለም ከርሱ ጋራ ለመሆን ራሳችንን ማዘጋጀት ነው። ስለዚህ ጌታህ በምን ቀን እንደሚመጣ አታውቅምና አንተም ነቅተህ መጠበቅ አለብህ! ይህን ልብ በል፡ *ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ። ያን ግን እወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ ቤቱም ሊቈፈር ባልተወም ነበር። ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና* (ማቴዎስ 24:42- 44)።

በእምነት የሆነን ኑሮ ለርሱ በመኖር፣ ርሱን በማገልገልና በስሙ መልካም ሥራዎችን በመሥራት ራሳችንን ዝግጁ ማድረግ አለብን። *እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን* (ኤፌሶን 2:10)።

## ቤተ ሰብ

አብዛኛውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ በሚል ስያሜ ትታወቃለች። እኛም የእግዚአብሔር ልጆች የሚል ስያሜ ተቀበልን።

Free digital copy from ServeNow

ገላትያ 6:10 ላይ *እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም <u>ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች</u> መልካም እናድርግ* ተብሎ ተጽፎ እናገናለን።

አክሎም ኤፌሶን 2:19 ላይ *እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋራ ባላገሮችና <u>የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች</u> ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።*

ደግሞም በገላትያ 3:26-28 ላይ እንዲህ የሚል ዐሳብ እናገኛለን፦ *በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤ ከክርስቶስ ጋራ አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።*

እውነተኛ አማኞች ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብነት በልጅነት ሥልጣን በኩል ገብተው የርሱ ቤተ ሰብ አካል ሆነዋል። ከዚህ የበለጠ መብት እና የባለቤትነት ስሜት የለም። እግዚአብሔርን እንደ አባታችን ከማወቅ የበለጠ ግላዊ ሊሆን የሚችል አንዳች ነገር አይኖርም። ይህም ለክርስቶስ ወንድሞች እና እኅቶች እንድንሆን ያደርገናል። ይህ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ እውነታ ከሰው ቤተ ሰብ እሳቤ በላይ ነው። ዘላለማዊ እውነታም ነው።

## ***የእውነት መሠረትና ዐምድ***

1 ጢሞቴዎስ 3:15 ላይ ሰዎች በእግዚአብሔር ቤት ያውም የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፣ የእውነት መሠረት እና ዐምድ ወስጥ እንዴት ያለ ባሕርይ ሊኖራቸው እንደሚገባ ይነግረናል።

አምዶች (ምሰሶዎች) የአንድን ሕንጻ መዋቅሮችን ይደግፋሉ። የሕንጻ መሠረቱ በጣም ወሳኝ ነው። ዐምዶች የደከሙ ከሆኑና መሠረትም በሥርዓቱ ካልተጣለ ሙሉው

Free digital copy from ServeNow

ሕንጻ የመውደቅ አደጋ ውስጥ ይሆናል። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ እና ጨውና ብርሃን መሆኗን ተግባራዊ ማድረግ አለባት። ይህም በዚህ ዓለም ውስጥ ከሚገኙ በብዙ ውሸቶችና የፈጠራ ወሬዎች መካከል የእውነት ዐምድ እና መሠረት ነው።

## *ማኅበረ ሰብ*

1 ጴጥሮስ 2:9 እናንተ … *የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ* ብሎ ይነግረናል።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ተከታዮች ማኅበረ ሰብ ናት። ቤተ ክርስቲያን ትልቅም ይሁን ትንሽ በኢየሱስ የተጠሩት እና የኢየሱስ የሆኑ የሰዎች ስብስብ ናት። አሁንም የምንኖርበት የየትኛውም ምድራዊ ማኅበረ ሰብ አባል ብንሆንም ዜግነታችን አሁን እንኳ ከሁሉም አስቀድሞ በሰማይ ነው! ፊልጵስዩስ 3:20 እንዲህ ያስታውሰናል። *እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን ርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን…* ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ማኅበረ ሰብ ናት።

## *መንፈሳዊያን ሠራዊት*

በ2 ጢሞቴዎስ 2:3 ሐዋርያው ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ *እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል* ይለዋል።

ቀጥሎም በዚሁ ጉዳይ ላይ በ2 ቆሮንቶስ 10:3-5 ላይ *በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን፥ እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም ዐሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን። ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን* ይላል።

Free digital copy from ServeNow

ደግሞም ጳውሎስ በኤፌሶን ላሉ አማኞች ሲጽፍ *በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሰራዊት ጋር ነው እንጂ።*

*ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ ርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም ዐሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ* (ኤፌሶን 6:10-18)።

ውጊያችን ከደም እና *ሥጋ ጋር* አይደለም። ውጊያችን ከዲያብሎስና ከአጋንንቱ ጋር የሚደረግ መንፈሳዊ ውጊያ ነው። የምንዋጋበት መንገድ ዓለም እንደምትዋጋው በሰው ሠራሽ የጦር መሣሪያ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል እና ተንበርክከን በጸሎት ነው! ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ትጥቅ በመልበስ እና የተሰጧት መንፈሳዊ ትጥቆችን በሙሉ በመጠቀም ሌሎች በኢየሱስ የሚገኘውን ነፃነት እንዲያውቁ ዕለት ተዕለት የሚኖሩ አማኞች መንፈሳዊያን ሰራዊት ስብስብ ነች!

## ***መንፈሳዊ ቤት እና ቅዱስ ክህነት***

በ1 ጴጥሮስ 2:4-5 *በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠና ክቡር ወደ ሆነው ወደ ሕያው*

Free digital copy from ServeNow

*ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችሁ፥ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ* እንደተባልን እናነባለን።

በሙሴ ሕግ እሥራኤላውያን ለእግዚኣብሔር የእንስሳትና ሌሎች መሥዋዕትን ያቀርቡ ነበር። የሌዊ ወገንም ለክህነቱ ሥራ የተለየ ማኅበረ ሰብ ነበር። ይህንንም ለእግዚአብሔር አምልኮ በተዘጋጀው ትክክለኛው የቤተ መቅደስ ሕንጻ ላይ ማድረግ ነበረባቸው። ይህም የእግዚአብሔር መገኘት የሚሆንበት ሥፍራ ነበር።

ነገር ግን አሁን፣ ኢየሱስ ከእኛ ጋራ በገባው አዲስ ኪዳን መሠረት፣ እኛ የእግዚአብሔር ሰዎች፣ የእግዚአብሔር መገኘት የሚኖርበት ቤተ መቅደሶች፣ መንፈሳዊ ቤቶች ነን! 1 ቆሮንቶስ 6:19- *ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን?*

እንግዲያው፣ እንደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፣ ቤተ ሰብ እና ካህናት፣ “በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን” ማቅረብ አለብን። እነዚያ መንፈሳዊ መሥዋዕቶች መላ ሕይወታችንን እና አካላችንን፣ ውዳሴያችንን እና ምስጋናችንን፣ መስጠትን፣ በጎ ማድረግን እና ርስ በርስ መረዳዳትን እንዲሁም ሌሎችን ያካትታሉ።

ሮሜ 12:1 እንዲህ ያበረታታናል፤ *እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ ርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።*

ዕብራውያን 13:15-16 ላይ ሲቀጥል *እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ*

Free digital copy from ServeNow

*የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በርሱ እናቅርብለት። ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።*

## የቤተ ክርስቲያን ዐላማ/ተግባር

### *የእግዚአብሔርን ምስጋና ማወጅ፡ አምልኮ*

ይህ ዐላማ በ1 ጴጥሮስ 2:9-10 ላይ ግልጽ ተደርጓል፤ *እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም። አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።*

ቤተ ክርስቲያን በሰማይ ላለው አምልኮ በምድር የምትታይ ትንሹ ምስል ናት (ራእይ 4፡5)። በሰማይ ያለው አምልኮ በእኛ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ምስጋና በማወጅ ላይ ያተኮረ ነው። በተለይ በክርስቶስ ስላደረገልን ምሕረት እግዚአብሔርን በማምለክ እና በማመስገን ላይ ያተኮረ ነው። በደሙ ቤዛችን የሆነውን ክርስቶስን ያከብራል፤ ይመሰክርማል።

ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘውን ቸርነት፣ ጸጋ፣ ምሕረት እና ቤዛነት ማወጅ አለባት። ርሱንና የከበረ ምስጋናውን በምድር ሁሉ ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግ ነው። አምልኮ የእግዚአብሔር ሰዎች አንድ ላይ በሚሰበሰቡበት ጊዜ ጉልህ ባሕርይ እና ተግባር መሆን አለበት። ለክርስቶስ ማንነት፣ መገኘት፣ ኃይል እና አቅርቦት እንሰጣለን።

### *ጸሎት*

ቆላስይስ 4:2 *ከማመስገን ጋር በጸሎት እየነቃችሁ ለርሱ ትጉ።*

1ኛ ጢሞቴዎስ 2:1-6 *እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥*

Free digital copy from ServeNow

*ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው። አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ ርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ ይላል።*

ጸሎት የቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት። በማንኛውም ጊዜ ስለ ሁሉም ነገር መጸለይ እና እንደ ቤተ ክርስቲያንም አካላት ለጸሎት በዐላማ መሰባሰብ አለብን።

## *የእግዚአብሔር ጥበብ እንድትታወቅ ማድረግ*

*ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፤ ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈጸመው የዘላለም ዐሳብ ነበረ* (ኤፌሶን 3:10-11)።

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንገዶች እና ጥበብ የሚገለጡበት እና የሚታወቁበት መንገድ ነው። ብዙ ገጽታ ያለው እና ለመረዳት የማይቻል የእግዚአብሔር ጥበብ የሚታየው እና የተበሰረው በቤተ ክርስቲያን፣ (በክርስቶስ በተዋጁት) በኩል ነው።

## *ሰዎችን የኢየሱስ ተከታዮች ማድረግ እና ማስተማር*

*ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ “ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ”* (ማቴዎስ 28:18-20)።

Free digital copy from ServeNow

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 4:11-16 ላይ *ርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌል ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።*

*እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሰፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም፥ ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ ርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤*

*ከርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።*

ቤተ ክርስቲያን የምትሰባሰብ ከዚያም የምትሄድ ናት። ጠንካራ፣ ጤናማ እና ጎልማሳ ሆና ለማደግ እና ለመበረታታት፣ ለመምከር፣ ለመታጠቅ እና ለማጎልበት "መሰባሰብ" ነው። ቁርጠኞች የሆኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮችን ለማፍራት ደግሞ "የምትሄድ" ናት። ቤተ ክርስቲያን ሌሎችን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ መጀመሪያ ደቀ መዝሙር መሆን አለባት። ደቀ መዝሙር ማለት ኢየሱስን ለመምሰል ከኢየሱስ የሚማር ነው። ራስህን ለክርስቶስ በመስጠት፣ ሌሎች ክርስቶስን እንዲመስሉ መርዳት ትችላለህ!

## *ተጠያቂነትን መለማመድ እና የቤተ ክርስቲያንን ተግሣጽ መፈጸም*

ማቴዎስ 18:15-20 *"ወንድምህም ቢበድልህ፥ ሄደህ አንተና ርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ፥ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው፤ ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት*

Free digital copy from ServeNow

*ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፤ እነርሱንም ባይሰማ፥ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት፥ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ።*

*እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል። ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።"*

ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱን አባል ተጠያቂነት እና ኃላፊነት እንዲሰማው ታደርጋለች። ኃጢአትን በሕይወታችንም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መታገስ ወይም ተቀባይነት እንዲኖረው መደረግ የለበትም። ኃጢአት በቀጥታና ኢየሱስ ባቋቋመው መርሕ እና ሂደት መሠረት መስተናገድ አለበት። እንደ እግዚአብሔር ልጆች እና የርሱ እንደራሴዎች፣ የክርስቶስን ምስክርነት በዓለም ፊት ልንጠብቅ ይገባል።

አንዳችን ለሌላችን ተጠያቂ ስንሆን እና በሕይወታችን እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚስተዋለውን ኃጢአት ለማስወገድ ስንሠራ፣ የኢየሱስ መገኘቱ እና ኃይሉ ደግሞም በረከቱ አብሮን እንደሚሆን ቃል ገብቶልናል። ይህን ሳናደርግ ብንቀር የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ከመበላሸቱም በላይ መሳቂያ እና መሳለቂያ እንሆናለን፤ ይህም ውጤት አልባነትን እና ፍሬ ቢስነት ያስከትላል።

## ቅዱሳት ምስጢራት

ቅዱሳት መጻሕፍት በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ ሊሳተፉባቸው ስለሚገባቸው ሁለት ወሳኝ ተግባራት ያስተምራሉ። የመጀመሪያው ጥምቀት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የጌታ ራት ነው።

Free digital copy from ServeNow

## ጥምቀት

ኢየሱስ በማቴዎስ 28:18-19 ለደቀ መዛሙርቱ *ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እ ንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው...*

ጥምቀት ለክርስቶስ የመታዘዛችን ማሳያ ተግባር እና የርሱ መሆናችን ማረጋገጫ ነው። በሞቱ እና በትንሣኤው መተባበራችንን፣ ደግሞም ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን እንደሞተ ለኃጢአት መሞታችንን የሚያሳይ ምስል ሲሆን በተጨማሪም ርሱ ለዐዲስ ሕይወት እንደተነሣ እኛም ለዐዲስ ሕይወት መነሣታችንን ማሳያ ነው። ሮሜ 6:3-4 *ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋራ አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በዐዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋራ አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከርሱ ጋራ ተቀበርን።*

ጥምቀት የግል እምነትን በክርስቶስ ኢየሱስ ጌታችን ላይ ማድረጋችንን ማመላከቻ ነው። በዐዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው አስረጅም ሰው መጀመሪያ በክርስቶስ ሲያምን ቀጥሎ መጠመቁ ነው። ለምሳሌ፡- በሐዋርያት ሥራ 18፡8 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን ለሌሎች ሰዎች ሲያካፍል ከቆሮንቶስ ሰዎች ምን ያህሉ እንደሰሙት እና እንደተጠመቁ ይናገራል።

## የጌታ እራት

በ1ኛ ቆሮንቶስ 11:23-26 ላይ ጳውሎስ ሲጽፍ *ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቈርሶም፡- “እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ*

Free digital copy from ServeNow

*የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት፡" አለ። እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፡- "ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት፡" አለ። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።*

የጌታ እራት በመስቀል ላይ ጌታ ስለ እያንዳንዳችን ኃጢአት የከፈለውን መሥዋዕት ያስታውሰናል። ደጋግመን ርሱ ላይ እንድናተኩር እና ስለ እኛ ያደረገውን እንድናስብ ይረዳናል።

## በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳችን ከሌላው ጋር እንዴት እንቀራረባለን?

*ርስ በርሳችሁ በክርስቶስ ፍቅር፣ መከባበር እና መገዛት*

*ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ*(ኤፌሶን 5:21)።

### ***ርስ በርስ ማገልገል***

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁላችንም በክርስቶስ እኩል ወንድሞች እና እኅቶች ነን። ሮሜ 12: 6-8 *እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤ አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር።*

1ኛ ቆሮንቶስ 12፡ 27-28 *እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ። እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ። እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ ርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዐይነት ልሳኖችንም አድርጎአል።*

Free digital copy from ServeNow

1ኛ ቆሮንቶስ 13ም በመቀጠል በልባችን እና በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታዎችን ስንለማመድ ፍቅር እንዴት ገዢ ሊሆን እንደሚገባው ይናገራል። ፍቅር ከሌለ ግን ራስ ወዳድነት፣ አለመቀባበል፣ ቅናት፣ ግጭት እና ሌሎችም ችግሮች ይከሰታሉ።

## ***አመራር***

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን አመራርን ይሰጣታል። ዕብራውያን 13፡17 ላይ *ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።* ይለናል።

## ***የዐዲስ ኪዳኑ "እንዳችሁ ሌላችሁን"***

1. *ርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ።* 1 ጴጥሮስ 1:22
2. *በወንድማማች መዋደድ ርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።* ሮሜ 12:10
3. *ርስ በርሳችሁ ተከባበሩ።* ሮሜ 12:10
4. *ርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ።* ሮሜ 12:16
5. *ርስ በርሳችሁ አትፈራረዱ።* ሮሜ 14:13
6. *ርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ።* ሮሜ 15:7
7. *ርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ።* ቆላስይስ 3:16
8. *ዕለት ዕለት ርስ በርሳችሁ ተመካከሩ።* ዕብራውያን 3:13
9. *ርስ በርሳችሁ ተመካከሩ አንዱም አንዱም ሌላውን ያንጸው።* 1 ተሰሎንቄ 5:11
10. *ርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ።* 1 ቆሮንቶስ 11:33
11. *ርስ በርሳቸው በትክክል ተሳሰቡ ።* 1 ቆሮንቶስ 12:25
12. *በፍቅር ርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።* ገላትያ 5:1
13. *ርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ።* ገላትያ 5:26
14. *ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም።*ገላትያ 6:2

Free digital copy from ServeNow

15. *ርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ።* ኤፌሶን 4:2
16. *ርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ።* ኤፌሶን 4:32
17. *እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።* ኤፌሶን 4:32
18. *በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ ርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ።* ኤፌሶን 5:19
19. *ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ።* ኤፌሶን 5:21
20. *ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር።* ፊልጵስዩስ 2:3
21. *ርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና።* ቆላስይስ 3:9
22. *ርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ።* ቆላስይስ 3:13
23. *ርስ በርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ይብዛ ይጨምርም።* 1 ተሰሎንቄ 3:12
24. *ርስ በርሳችን እንተያይ።* ዕብራውያን 10:24
25. *ርስ በርሳችሁ አትተማሙ።* ያዕቆብ 4:11
26. *ርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ።* ያዕቆብ 5:9
27. *ርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ።* ያዕቆብ 5:16
28. *አንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ።* ያዕቆብ 5፡16
29. *ያለ ማንጐራጐር ርስ በርሳችሁ እንግድነትን ተቀባበሉ።* 1ኛ ጴጥሮስ 4:9
30. *እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ ርስ በርሳችሁ አገልግሉ።* 1ኛ ጴጥሮስ 4:10
31. *ሁላችሁም ርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ።* 1ኛ ጴጥሮስ 5:5
32. *እናንተ ደግሞ ርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል።* ዮሐንስ 13:14

## የጤናማ ቤተ ክርስቲያን ምልክቶች

በራእይ መጽሐፍ ምዕራፍ 2-3 በወቅቱ ለነበሩት ሰባት አቢያተ ክርስቲያናት እንዲያደርስ ኢየሱስ ለሐዋርያው

Free digital copy from ServeNow

ዮሐንስ መልእክት ሲሰጥ እንመለከታለን። ከነዚህ ለሰባቱ አቢያተ ክርስቲያናት የተጻፉ ሰባት ደብዳቤዎች ጤናማ እና ጤናማ ያልሆኑ የአቢያተ ክርስቲያናት መገለጫዎችን ልብ ልንል እንችላለን። እንዲህ ይነበባል፦

*በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ በቀኝ እጁ ሰባቱን ከዋክብት የያዘው በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው እንዲህ ይላል፦ ሥራህንና ድካምህን ትዕግሥትህንም አውቃለሁ፤ ክፉዎችንም ልትታገሥ እንዳትችል፥ እንዲሁም ሳይሆኑ፦ ሐዋርያት ነን፡ የሚሉቱን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ፤ ታግሠህማል፥ ስለ ስሜም ብለህ ጸንተህ አልደከምህም።*

*ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፡ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና። እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ። ነገር ግን ይህ አለህ፤ እኔ ደግሞ የምጠላውን የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃልና።*

*መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።*

*በሰምርኔስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው፡ እንዲህ ይላል፦ መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ፥ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ፤ የሰይጣንም ማኅበር ናቸው እንጂ አይሁድ ሳይሆኑ፦ አይሁድ ነን፡ የሚሉት የሚሳደቡትን ስድብ አውቃለሁ። ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም*

Free digital copy from ServeNow

*መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።*

*መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም።*

*በጴርጋሞንም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ያለው እንዲህ ይላል፦ የሰይጣን ዙፋን ባለበት የምትኖርበትን አውቃለሁ፤ስሜንምትጠብቃለህ፥ሰይጣንምበሚኖርበት፥ በእናንተ ዘንድ የተገደለው የታመነው ምስክሬ አንቲጳስ በነበረበት ዘመን እንኳ ሃይማኖቴን አልካድህም።*

*ዳሩ ግን ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንዲሴስኑ በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን ሊያኖርባቸው ባላቅን ያስተማረ የበልዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በዚያ ከአንተ ጋራ ስላሉ፥ የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ። እንዲሁ የኒቆላውያንን ትምህርት እንደ እነዚህ የሚጠብቁ ሰዎች ከአንተ ጋራ ደግሞ አሉ። እንግዲህ ንስሐ ግባ፤ አለዚያ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፥ በአፌም ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ።*

*መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፥ ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፥ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ ዐዲስ ስም ተጽፏል።*

*በትያጥሮንም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዓይኖች ያሉት በእቶንም የነጠረ የጋለ ናስ የሚመስሉ እግሮች ያሉት የእግዚአብሔር ልጅ እንዲህ ይላል፦ ሥራህንና ፍቅርህን እምነትህንም አገልግሎትህንም ትዕግሥትህንም ከፊተኛውም ሥራህ ይልቅ የኋለኛው እንዲበዛ አውቃለሁ።*

*ዳሩ ግን፦ ነቢይ ነኝ፡ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና*

Free digital copy from ServeNow

*የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ንስሐም እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ከዝሙትዋም ንስሐ እንድትገባ አልወደደችም። እነሆ፥ በአልጋ ላይ እጥላታለሁ፥ ከርስዋም ጋራ የሚያመነዝሩትን ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ፤ ልጆችዋንም በሞት እገድላቸዋለሁ፤ አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ኵላሊትንና ልብን የምመረምር እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ፥ ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ።*

*ዳሩ ግን ይህን ትምህርት ለማትይዙ ሁሉ የሰይጣንንም ጥልቅ ነገር እነርሱ እንደሚሉት ለማታውቁ ለእናንተ በትያጥሮን ለቀራችሁት እላለሁ፤ ሌላ ሸክም አልጭንባችሁም፥ ነገር ግን እስክመጣ ድረስ ያላችሁን ጠብቁ።*

*ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፥ በብረትም በትር ይገዛቸዋል፥ እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ፤ የንጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ።*

*መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።*

*በሰርዴስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስትና ሰባቱ ከዋክብት ያሉት እንዲህ ይላል፦ ሥራህን አውቃለሁ ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ ሞተህማል።*

*ሥራህን በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን፥ ሊሞቱም ያላቸውን የቀሩትን ነገሮች አጽና።*

*እንግዲህ እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ፥ ጠብቀውም ንስሐም ግባ። እንግዲያስ ባትነቃ እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም።*

*ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ጋራ አሉ፥ የተገባቸውም ስለ ሆኑ ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ*

Free digital copy from ServeNow

*ጋር ይሄዳሉ። ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።*

*በፊልድልፍያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡- የዳዊት መክፈቻ ያለው፣ የሚከፍት፥ የሚዘጋም የሌለ፣ የሚዘጋ፥ የሚከፍትም የሌለ፣ ቅዱስና እውነተኛ የሆነው ርሱ እንዲህ ይላል፡- ሥራህን አውቃለሁ፣ እነሆ፥ በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና፥ ስሜንም አልካድህምና።*

*እነሆ፥ አይሁድ ሳይሆኑ፡- አይሁድ ነን፡ ከሚሉ ነገር ግን ከሚዋሹ ከሰይጣን ማኅበር አንዳንዶችን እሰጥሃለሁ እነሆ፥ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ።*

*የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ።*

*እነሆ፥ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ፤ ማንም አክሊልህን እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ። ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዐምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፤ የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም፥ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፥ አዲሱንም ስሜን በርሱ ላይ እጽፋለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።*

*በሎዶቅያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡- አሜን የሆነው፥ የታመነውና እውነተኛው ምስክር፥ በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው እንዲህ ይላል፡- በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን*

Free digital copy from ServeNow

*አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር። እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው።*

*ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም፡ የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፥ ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ፥ ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፥ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኵል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ።*

*እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ። እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ ርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋራ እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋራ ይበላል።*

*እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።*

*እስቲ ከዚሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በአዎንታዊ ዕሳቦች እንጀምር!*

## *ኤፌሶን – ሥራ፣ ትጋት፣ (Discernment) ልየታ፣ ቁርጠኝነት*

ኢየሱስ በመጀመሪያ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ስለ መልካም ሥራዋ አሞግሷታል። አንደኛው የጤናማ ቤተ ክርስቲያን መገለጫ ሰዎች ማገልገላቸው ነው። ኢየሱስ እንዲያገለግሉት ሳይሆን ራሱ ሊያገለግል መጥቷል፤ ጤናማ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን አርዓያ የምትከተል ናት። የድርጊት ቤተ ክርስቲያን ናት።

Free digital copy from ServeNow

ሁለተኛው ኢየሱስ በኤፌሶን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ለብርቱ ሥራዋ፣ ለጽናቷ ወይም ለትጋቷ እና ለሥርዓቷ ተሞግሳለች። የጤናማ ቤተ ክርስቲያን ሌላኛው መገለጫ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ሰነፍ አለመሆኗ ነው። ከእግዚአብሔር ጸጋን መቀበል ብቻ ሳይሆን ያው ጸጋ እግዚአብሔር ሊሠራ የወደደውን እንዲፈጽም ደግሞም በእነርሱ በኩል እንዲሠራ ማድረግ ነው። *ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ሁልጊዜ እንደ ታዘዛችሁ፥ በእናንተ ዘንድ በመኖሬ ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ስርቅ፥ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና* (ፊልጵስዩስ 2:12-13)። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ሥራዋን አታቋርጥም።

ሦስተኛው ኢየሱስ በኤፌሶን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ያሞገሰበት ስለ መለየት ሥራዋ ነው። የትኛውንም ነገር ወይም በክርስቶስ ስም የመጣውን ማንንም ሰው በጭፍን አልተቀበሉም። በክርስቶስ ስም የመጡትን ሁሉ ፈትነዋል፤ ሐሰተኞችንም አልታገሡም። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን የመለየትን ጸጋ በመጠቀም በክርስቶስ ስም የሚመጣ ወይም የተላከ ሁሉ እውነተኛ እንዳልሆነ ትገነዘባለች። ኢየሱስም በማቴዎስ 24፡4 *ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ* ብሏል።

አራተኛው ኢየሱስ በኤፌሶን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ያሞገሰበት ስለ ቁርጠኝነቷ ነበር። ለኢየሱስ ክርስቶስ ካላቸው ቁርጠኝነት የተነሣ መከራን ተቋቁመዋል፤ ደግሞም አልደከሙም ነበር። ጤናማ የሆነች ቤተ ክርስቲያን በተቃውሞ፣ በችግር ወይም በስደት አትሸመደመድም፤ ደግሞም ለክርስቶስ ያላትን ታማኝነቷን አታመቻምችም። ተቃውሞዎችን፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እና ተግዳሮቶችን ክርስቶስ ላይ በመጣበቅ በጽናት ታልፋለች።

Free digital copy from ServeNow

## *ሰምርኔስ – ታማኝነት*

በሰምርኔስ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በውጫዊ ሁኔታዋ ሞልቶላት የተትረፈረፈ ወይም በብልጽግና የምትታወቅ አልነበረችም። ሆኖም በመከራና በድህነት ብትሆኑም በመንፈሳዊ ነገር ሀብታሞች ስለ ነበሩ ኢየሱስ አሞግሷቸዋል። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ውጫዊ ገጽታዋ ወይም ሁኔታዋ ሳይገድባት በታማኝነቷ የምትገለጥ ነች።

## *ጴርጋሞን – ቁርጠኝነት*

ኢየሱስ ጴርጋሞን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ የሰይጣን ዙፋን ያለበት ከተማ ውስጥ ብትሆንም በኢየሱስ ማንነት ላይ ላሳየችው ቁርጠኝነት እና በዚያው እውነት ላይ በመቆየቷ አሞግሷታል። ምንም እንኳ አንቲጳስ ከመካከላቸው በኢየሱስ ላይ በነበረው እምነቱ ምክንያት ቢገደለም በእነርሱ ጸንተው መቆም ተደንቋል።

## *ትያጥሮን – መሰጠት*

ኢየሱስ በትያጥሮን ላለች ቤተ ክርስቲያን ሥራቸውን፣ ፍቅራቸውን እና እምነታቸውን፣ አገልግሎታቸውን እና ጽናታቸውን እንዲሁም ከቀድሞው የበለጠ እየሠሩ እንደነበሩ ማወቁን አስረግጦ ተናግሯል። ጤናማ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለጌታ ያላትን ታማኝነት በተግባር እና በአመለካከታቸው ታሳያለች። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ቅንዓቷና ተግባሯ እየጨመረ፣ በቃለ ስሜት እና በአገልግሎት ታድጋለች።

## *ሰርዴስ – ንጽሕና*

ኢየሱስ ለአብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የሚነቅፍባቸው እንደነበረው ብነግራቸውም፣ በሰርዴስ ውስጥ ለነበረችው ግን ለቃሉ በመታዘዝ ለእርሱ ታማኝ ሆነው የቆዩ ጥቂቶች እንደነበሩ ተናግሯል።

Free digital copy from ServeNow

***ፊላደልፍያ – ጽናት***

ኢየሱስ በፊላደልፊያ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በፈተና ውስጥ ስላሳዩት ጽናት አድንቋቸዋል። *ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና፥ ስሜንም አልካድህምና* አላቸው። ደግሞም *የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ* ብሎ ተናገራቸው።

ብዙ የተለመደ ባይሆንም ጤናማ ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ያሉ ምእመናን በዚህ ምክንያት ሲሰደዱ የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቃ ትጠብቃለች። የኢየሱስ መሆናቸውን ባለመካድ እና በርሱ ላይ ያላቸው እምነት በሕይወታቸው ውስጥ የሚያመጣውን ማንኛውንም ፈተናም ሆነ መዘዝ ውስጥ በትዕግስት ጸንተው ይቆማሉ። ምንም እንኳ ድካም ቢሰማቸውም በኢየሱስ ላይ ተጣብቀው የበረቱ ይሆናሉ።

***ሎዶቅያ – ትሕትና እና ፍቅር***

ኢየሱስ በሎዶቅያ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን የሚያሞግስበት አንዳች አዎንታዊ ነገር አልነበረውም። በሀብታቸው ላይ ከነበራቸው የውሸት ደኅንነት የተነሣ ትዕቢተኞች፣ የተታለሉ፣ ግድ የለሾች እና ስለ እውነተኛ መንፈሳዊ ጉዳዮች የታወሩ ነበሩ።

ጤናማ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ግን በጌታ ላይ የምትደገፍ እና ጌታንም አብልጣ የምትወድ ሆና ትቀጥላለች። ቁሳዊ ሀብት በመንፈሳዊ ነገር ሁሉ ሀብታም ከመሆን ጋር አንድነት እንዳለው አድርገው አያስቡም።

***ኤፌሶን – የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃል***

በኤፌሶን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ብዙ መልካም ሥራዎች ስለ ነበሯት፣ ኢየሱስ በግልጽ አሞግሷታል። ሆኖም ግን አንዳች የሚነቅፍባቸው ነገር ነበረው፣ በሁሉም ተግባሮቻቸው

Free digital copy from ServeNow

መካከል በፍላጎት ብቻ መሄድ መጀመራቸውን ነው። ለኢየሱስ የነበራቸውን ፍቅር አጥተዋል!

ለዚህም ችግር የሚበጅ መፍትሔ ተሰጥቷቸዋል። ከየትኛው ከፍታ እንደ ወድቅህ አስብ! በመጀመሪያ ታደርጋቸው የነበሩትን ሁሉ አስታውስ እና ንስሐ ግባ። ለኢየሱስ የነበረንን የቀደመ ፍቅር እንደገና ለማግኘት ልናስታውስ፣ ንስሐም ልንገባ እና እንደገና ልንተገብር ይገባል። ለዚህች ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውም ማስጠንቀቂያ ይህንን ባታደርግ መቅረዟ ከሥፍራው ይወሰዳል። ለኢየሱስ ፍቅር ማጣት ማለት ውጤታማነትን፣ ፍሬአማነትንና ተጽእኖ ማምጣትን ማጣት ማለት ነው።

ጤናማ ቤተ ክርስቲያን በተቃራኒው በኢየሱስ ላይ ጥገኛ በመሆን በጌታዋ ፍቅር ላይ የምትጸና ትሆናለች። ቁሳዊ ሃብትን ከመንፈሳዊ በረከት እኩል አትመለከትም።

አሉታዊ ጎኑ ደግሞ አንዲት ጤናማ ቤተ ክርስቲያን መናዘዝ እና ንስሐ መግባት ይጠበቅባታል።

## *ሰምርኔስ – ፍርሃት*

ኢየሱስ በሰምርኔስ ላለች ቤተ ክርስቲያን ምንም ተግሣጽ አልነበረውም፣ ሊደርስባቸው ያለውን መከራ እንዳይፈሩ የሚያበረታታ እና የሚያጽናና ብቻ ነበር። ካልተጠነቀቅን በስተቀር ፍርሃት ጤናማ እና ጠንካራ የሆነችን ቤተ ክርስቲያን አሽመድምዶ ሽባ ሊያደርጋት ይችላል። ምንም ዐይነት ዋጋ ቢያስከፍልም መፍራት ሳይሆን በርሱ ላይ ያለንን ታማኝነት እንድናጸና ኢየሱስ ይፈልጋል።

ጤናማ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ምስክርነት ደፋር እና ጀግና የሆነች ነች። ስለ ድፍረት ልንጸልይ ያስፈልጋል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንኳ ስለ ድፍረት እና ጥንካሬ እንዲጸለይለት ጠይቋል! ኤፌሶን 6፡19-20 እንዲህ ይላል *ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን*

Free digital copy from ServeNow

*በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፤ ስለ ወንጌልም በሰንሰለት መልእክተኛ የሆንሁ፥ መናገር እንደሚገባኝ ስለ ርሱ በግልጥ እናገር ዘንድ ለምኑ።*

## ጴርጋሞን – ጣዖት አምልኮ እና ርኩሰት

በጴርጋሞን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኢየሱስ ስለ ጣዖት አምልኮና ስለ ዝሙት የገሰጻቸው ሰዎች ነበሩ። በተደላደለ ዓለማዊ ሕይወት ውስጥ ይኖሩ ነበር። ሌሎች አማልክትን በሚያከብሩ ተግባራት እና በዝሙት ርኩሰት ባሕርያት ውስጥ ይሳተፉ ነበር። ራሳችንን ከጣዖት አምልኮ እና ከርኩሰት ልንጠብቅ ያስፈልጋል። በዙሪያችን ካሉ ዓለማዊ መንገዶች ጋራ መሄድ ሳይሆን በአእምሮአችን መታደስ መለወጥ ይጠበቅብናል (ሮሜ 12፡ 1-2)።

## ትያጥሮን –ሐሰተኛ መምህራንን መታገስ

በትያጥሮን በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው ችግር የሰዎቹ በጣዖት አምልኮ እና ርኩሰት ውስጥ መሆን ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያስቷቸውን ሰዎች መታገሳቸው ነበር። የሐሰት ትምህርት እና ወደ ኃጢአት የሚመሩ አስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም።

## ሰርዴስ – መንፈሳዊ እንቅልፍ

በሰርዴስ ያለችው ቤተ ክርስቲያን የሕያውነት ሙገሳ የነበራት ስትሆን ኢየሱስ ግን በእውነተኛ ሁኔታቸው የሞቱ እንደሆኑ ተናግሯል። እንዲነቁና የቀረውንና ሊሞት የነበረውን እንዲያጠናክሩ ጠራቸው። የሰሙትን እንዲያስቡና እንዲታዘዙ ደግሞም ንስሐ እንዲገቡም መከሯቸዋል።

የጤነኛ ቤተ ክርስቲያን አባላት ቃሉን ሰሚዎች ብቻ አይደሉም፣ ነገር ግን ቃሉን በተግባር የሚያውሉትም እንጂ። ኢየሱስን ጌታ እንደሆነ ብቻ የሚያስቡት ሳይሆኑ እንደ ጌታቸውም የሚታዘዙት ናቸው።

Free digital copy from ServeNow

***ፊላደልፍያ – ተስፋ መቁረጥ***

ኢየሱስ በፊላደልፍያ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን የሚገስጽበት አንዳች ምክንያት አልነበረውም። ነገር ግን ማንም አክሊላቸውን እንዳይወስድባቸው ያላቸውን ነገር አጽንተው እንዲይዙ አበረታታቸው። አብያተ ክርስቲያናት ከሚያጋጥሟቸው ፈተናዎች አንዱ ከሚያስጨንቋቸው ግብዞች እና ውሸታሞች የተነሣ ተስፋ መቁረጥ እና ወደ ኋላ መመለስ ነው። ኢየሱስ በከፈታቸው በሮች ስለ ርሱ እንድንጸና እንጂ ከሌሎች ሰዎች ድርጊት የተነሣ በተስፋ መቁረጥ ስሜት እንዳንሸነፍ ይልቁንም ለርሱ ምስክሮች እንድንሆን ጠርቶናል።

***ሎዶቅያ – መንፈሳዊ በራድነት (መንፈሳዊ እንቅልፍ)***

ለዚህችቤተክርስቲያንበራድነትመፍትሔየሚሆኑዐሳቦችበዚህ አንቀጽ ተዘርዝረዋል። ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ፥ ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፥ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኵል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ። እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ። እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ ርሱ እገባለሁ ከርሱም ጋራ እራት እበላለሁ ርሱም ከእኔ ጋራ ይበላል።

**ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ድል አድራጊ ቤተ ክርስቲያን ናት!**

ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ከተግዳሮት ነጻ የሆነች ሳትሆን መሰናክሎችን ሁሉ ያሸነፈች ናት። ድል ለነሣው የሚገባ ሽልማት እንዳለ ኢየሱስ ቃል ገብቷል። የሐዋርያት ሥራ 2፡ 42-47 ስንመለከት የቀደመችውን ቤተ ክርስቲያን ገጽታ ያሳየናል፤ እንዲህ ይነበባል። *በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር። ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ*

Free digital copy from ServeNow

*ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ። ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር። በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።*

## ***ዘጠኝ የጤናማ ቤተ ክርስቲያን መለያዎች***

- ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸው መሰጠት (ቅዱሳት መጻሕፍት)
- በክርስቶስ ርስ በርስ ያላቸው መቀባበል (ኅብረት)
- እንጀራን በጋራ መቁረስ (የጌታ ራት)
- በጸሎት መትጋት
- እግዚአብሔርን እና የመንፈሱን አሠራር መፍራት
- አንድነት እና ኅብረት
- ልግስና፣ መስጠት እና መስዋዕትነት
- አምልኮ
- የሚድኑት ቁጥር መጨመር እና የቤተ ክርስቲያን ዕድገት

ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ለኢየሱስ ደቀ መዝሙርነት ራሳቸውን የሰጡበት፣ ለእግዚአብሔር ቃል፣ ርስ በርሳቸው፣ ለኅብረት፣ ለጸሎት፣ ለመስጠትና አምልኮ የሚተጉባት፣ የእግዚአብሔርን በረከቶች የሚለማመዱባት ናት። በእግዚአብሔር ሐለዎት ውስጥ መፈራቱ ይስተዋላል። መንፈስ ቅዱስም በኃይለኛ እና ተዓምራዊ በሆነ መንገድ ይሠራል። በክርስቶስ የሆነ ኅብረት ይኖራል። የሚድኑትን ሰዎች እንኳ እግዚአብሔር ዕለት ዕለት ወደ እነርሱ ኅብረት ይጨምራል። የርሱ ቤተ ክርስቲያን እየበዛች፣ ጤናማ እና ብርቱም እየሆነች እንድትቀጥል ጸሎቴ ነው!

Free digital copy from ServeNow

## ለውይይት እና ግብረ መልስ የሚሆኑ ጥያቄዎች

- ስለ ቤተ ክርስቲያን ምንነት ምን ተማርህ? ምንስ ነች?

- አንድ ሰው ኢየሱስ በመገንባት ላይ ያለው ቤተ ክርስቲያን አካል እንዴት መሆን ይችላል?

- የትኛው የቤተ ክርስቲያን መልክ የተሻለ ትርጉም ይሰጥሃል? ለምን?

- ስለ ቤተ ክርስቲያን ዐላማ ስታስብ በግልህ የትኛው ላይ ብታተኩር ትመርጣለህ?

- “ርስ በርስ” ከሚሉት አሳቦች ውስጥ የትኛውን ታስቀድማለህ? ለምን?

- ኢየሱስ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተናገራቸው ቃላት የትኞቹን አዎንታዊ ገጽታዎች ስለ ቤተ ክርስቲያንህ እውነት እንደሆኑ ታስባለህ?

- ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ከተሰጡት ተግሣጾች መካከል ላለህባት አጥቢያ ተግባራዊ የሚሆን እና ለንስሐ የሚጋብዝ ወይም ለውጥ የሚአሻው የትኛው ነው?

- በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ በሥራ ላይ አለ የምትለው የጤናማ ቤተ ክርስቲያን መለያዎች የትኞቹ ናቸው?

- ከዘጠኙ የጤናማ ቤተ ክርስቲያን መለያዎች ውስጥ ባለህበት አጥቢያ ቢሻሻሉ የምትላቸው እና አንተም በለውጡ ሂደት ውስጥ መወጣት የሚገባህ አዎንታዊ ቅድመ ሥራ የትኛው ነው?